# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 69 ጳጉሜ 5 ቀን 2001 ዓ.ም

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

# የግንቦት 7 ሊ/መንበር፣ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የመልካም ምኞት መግለጫና የአዲስ አመት የትግል ጥሪ አስተላላፉ።

በተለያዩ ካሴቶች፣ሲዲዎች፣ ዌብሳይቶችና ሬዲዮ የሚሰራጨውና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ይሰማዋል ተብሎ የሚጠበቀው የሊ/መንበሩ መልእክት፣ ኢትዮጵያውን ያለፈውን አመት ገምግመው በአዲሱ አመት ስለሚወስዱት እርምጃ በዝርዝር የሚናገር ነው።

ሊ/መንበሩ ንግግራቸውን የሚጀምሩት ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ ነው፤ “ከቀድሞው አመት በተሻለ ሕዝባችን ጠግቦ በላ? ልጆቹን የተሻለ መገበ? ገበሬው ከችጋር ተላቀቀ? ከተሜው ሰርቶ አደር አለፈለት? የመንግስት ሰራተኛው ተመቸው? ነጋዴው የተሻለ አተረፈ፤ ንግዱ ተሙዋሙዋቀ? ባጠቃላይ ኑሮ ካለፈው አመት የተሻለ ነበር? ካልሆነስ የኢኮኖሚ ችግሩ ሁላችንንም እንደዜጎች በእኩልነት አጠቃን? የሀብት ክፍፍሉስ ከቀድሞው በተሻለ የተመጣጠነ ነበርን? ኑሮአችን የበለጠ ዘምኖአል፤ ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር በመላመድ የወደፊቱ ሕይወታችንን ከሌላው አለም ጋር ወደሚቀራረብበት አቅጣጫ እየመራነው ነው? ልጆቻችን በሚያገኙት የትምህርት ጥራት የተነሳ ከተቀረው አለም ልጆች ጋር በእውቀት እየተቀራረቡ ነው?የአዲሱን ሺኛ የመጀመሪያ አመት ስናገባድድና አዲሱን ስንቀበል በተሻለ መብታችን ተከበረ? የተሻለ ነፃነት ተሰማን? የተሻለ የዜግነት ስሜት፤ የእኩልነት ስሜት ተሰማን? ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ተጠጋን? የተሻለ ዳኝነት አገኘን? አሁን ከቀድሞው የተሻለ ደህንነትና ሰላም ይሰማናል? አገራችን ከጦርነት ተላቃለች? ማህበረሰባችን ውስጡ ጤነኛ ነው? ከቀድሞው የተሻለ ደህንነትና ሰላም ይሰማናል? አገራችን ከጦርነት ተላቃለች? ማህበረሰባችን ውስጡ ጤነኛ ነው? በማህበራችን ውስጥ የይቅርታ ስሜት ሰፍኗል? **ወደ ገጽ 3 ዞሯል**



ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሊ/መንበር



## የግንቦት7 ድምጽ የአዲስ ዓመት መልእክት

እንኳን ከአንድ የትግል ዘመን ወደ ሌላ የትግል ዘመን አሸጋገረን።

2001 ዓም ኢትዮጵያ አገራችንና ሕዝባችን በበርካታ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ያለፉበት ዓመት ነበር። የግንቦት7 ድምጽ ሣምንታዊ ጋዜጣችንም የኢትዮጵያን ሁኔታዎችን ተከታትላ በመዘገብ በወያኔ ለታፈነው ሕዝባችን አማራጭ የመረጃ ምንጭ ለመሆን በቅታለች። በአዲሱ ዓመት ደግሞ ከዚህ የበለጠ ለመሥራት ታጥቃ ተነስታለች።

ወያኔ 2001 ዓምን የጀመረው "ድህነትን ተረት እናደርጋለን" በሚል አስደናቂ መፈክር ነበር። ኢትዮጵያዊ ጠግቦ ካደረ ስለሙብት ደንታ የለውም ብሎ ወያኔ ስለሚያምን የጥጋብ ወሬ ሲያራግብ፤ ሚሊየነር ስለሆኑ ገበሬዎች ሲያወራ ወራት አሳለፈ። ዓመቱ አጋማሽ ላይ ግን "ድህነትን ተረት እናደርጋለን" ራሱ ተረት ሆነ። በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ሳይቀር በቀን ሁለቴ መብላት የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሰ። የወያኔ መሃይም ካድሬዎች እንድ እድገት ማሳያ ይመለከቷቸው የነበሩ የሕንፃዎች ግንባታም ባለበት ቆሙ። ለጎረቤት አገራት ስለሚሸጥ የመብራት ኋይል ብዛት እጅግ ብዙ ጉራ ቢነዛም፤ ከተሜው ዓመቱ ያሳለፈው ሻማ በመወደዱ በኩራዝ ነው። ክረምት ዝናብ ቢዘንብም የሌሉ ግድቦችን ግን መሙላት አልቻለም። ወደ አስራ አራት ሚሊዮን የሚጠጋ ብዛት ያለው ሕዝብ ተራበ። የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ወያኔዎች ሃብት እያስግበሰበሱ በውጭ አገራት ባንኮች ማጠራቀም ቀጥለዋል። የሕዝብ መራብ ለወያኔ የማይነጥፍ የገቢ ምንጭ በመሆኑ ኤፈርትና ጭፍሮቹ የአገሪቷን ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረዋል። አሁን ደግሞ ለም የገጠር መሬቶችን ለባእዳን በመሸጥ ባላገሩን አገር አልባ አድርገው በሃብት ሊዋኙ አሰፍስፈዋል።

በፓለቲካው መስክ በአጠናቀቅነው ዓመት ወያኔ በርካታ እብደቶችን አስመዝግቧል።

1. ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በማይረባ ሰበብ ለእድሜ ልክ እስር በመዳረግ እብሪቱን አሳየ፤
2. አሳሪ የመያድ ሕግ በማውጣት ለጋሾቹን አስቀይሞ የእንጀራ ገመዱን አሳጠረ፤
3. ሕግ አልባነትን የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ ብሎ በማወጅ ዱርዬነቱን አስመሰከረ፤
4. አባል ማብዛት ያድን መስሎት ሁሉንም ሰው ፎርም በማስሞላት ድርጅቱን ወደ ስለላ መረብነት ቀየረ፤
5. ከፍተኛ የሲቪልና የጦር ሠራዊቱ የሥልጣን እርከኖች በአንድ ዘውግ ተወላጆች በማስያዝ ለዘረኛ ፓሊሲው መዋቅራዊ መሰረት ቢዘረጋም ከብርገጋ ግን አላስጣለውም። በርካታ ዜጎቻችን መንግሥቴን ልትገለብጡ ነበር፤ ልትገድሉን አሲራችኋል በሚል ክስ አስሮ እያሰቃየ ነው፤
6. ከሶማሊያ ወጣሁ ብሎ ባወጀ ማግሥት መሃል ሶማሊያ ውስጥ ገብቶ ሲገድል ይገኛል፤
7. በኦጋዴን የሚያካሄደው ጭፍጨፋ ከመገናኛ ብዙሃን መሸፈን የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

በማኅበራዊው መስክ ወያኔ በ2001 ዓም የሃይማኖት ጦርነት እንዲቀሰቀስ ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም። በተለይ በአዲስ አበባ ካድሬዎቹን የመነኩሴ ካባ አልብሶ ነቢዩ መሃመድን ማዘለፉ፤ በደሴ ክርሲቲያኖችን መጨፍጨፉና በሞስሊሞች ማሳበቡ፤ የኦርቶዶክስ ጳጳሳትን እርስበርስ ማጋጨቱ ተጠቃሽ ክንውኖች ናቸው። ከሃይማኖት ቅራኔው ጎን ለጎን የጎሳ ፍጅት ለመቀስቀስ ወያኔ በብርቱ ጥሯል። በዓመቱ ውስጥ ከ200 በላይ ትላልቅና ትናንሽ የጎሳ ግጭቶች ተመዝግበዋል። አሁን ደግሞ የጎሳ ቅራኔው ከፓለቲካ ጋር እንዲያያዝ በማድረግ የፓለቲካ ፓርቲዎች በከተሞች ውስጥ እንኳን የሚጠሩትን ስብሰባዎችን ማስበጥበጥ ጀምሯል። የሃይማኖትና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስጋት ቦታዎች ሁነው ነው ዓመቱ ያለፈው።

በዓለም ዓቀፍ ግኑኝነት ረገድ ዓመቱ ወያኔ በርካታ ኪሳራዎችን ያስመዘገበበት ነበር። የዓለም ዓቀፍ የዘር ማጥፋት ተከላካይ ድርጅት መለስ ዜናዊ በዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲከሰስ የዓለም ዓቀፍ ፍርድ ቤትን በደብዳቤ መጠየቁ የመለስን ስብእና እርቃኑን ያስቀረ ክስተት ነው። የዓለም ሃብታም ስምንት አገሮች በለንደን ባደረጉት ስብሰባ መለስ አፍሪካን ወክሎ እርዳታ እንዲለምን ቢላክም ከመላው አውሮፓ የተሰባሰቡ ኢትዮጵያዊያን ቅሌት አከናንበው እንዲመለስ አድርገውታል። ወያኔ የአሜሪካ የምርጫ ውጤትን የመገልበጥ አቅም ስለሌለው የማይፈልገው እጩ ተመርጦበት አብዷል። በቅርቡ አይጋ ፎረም የወያኔ ድረ ገጽ የፕሬዚዳንት ኦባማን አስተዳደር "ደግሞ ለኔግሮ መንግሥት ..." ሲል ማጣጣሉ የደረሰበት ዝቅጠት ከማሳየቱ በላይ ከአቅጣጫው ቁጣ አስነስቶበታል። የአሳለፍነው ዓመት በአሜሪካ፣ በእንግሊዝና አውሮፓ ፓርላማዎች ስለ ወያኔ አምባገነንነት በርካታ ጉባዬዎች የተደረጉበትና የዓለም ታላላቅ መሪዎች የመለስን አምባገነንነት፣ ዘራፊነት፣ ውሸታምነትና ጨፍጫፊነት በግለጽ የተረዱበትና የማግለለ እርምጃ መውሰድ የጀመሩበት ወቅት ነው።

በኢትዮጵያ የፓለቲካ ታሪክ ውስጥ በዓይነቱ ልዩ የሆነው ግንቦት7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የአንድ ዓመት ጨቅላ ቢሆንም በዚህ የምሥረታ ዓመቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከመሠረቱ ለውጦታል። ግንቦት7 ራሱ የመንግሥትን ሥልጣን ለመያዝ ዓላማ አድርጎ አለመነሳቱ ይልቁንስ ወያኔን የመጨረሻው አምባገነን በማድረግ በሁሉም ደረጃዎች ላይ ያሉ የሥልጣን እርከኖች በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ብቻ የሚያዙበት ሥርዓት አመቻች መሆኑ፤ አሁን ዋነኛ ትኩረታችን ወያኔን ማስወገድ ላይ እንዲሆን ማድረጉ እና ሁሉንም የትግል አማራጮች ለመጠቀም ዝግጁ መሆኑ ባጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ተሰሚነት ያገኘ ድርጅት ለመሆን አስችሎታል።

የግንቦት7ን የአለፈው ዓመት ሥራዎችንበሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ማጠቃለል ይቻላል።

1. ግንቦት7 በሃገር ውስጥም በውጭ አገራትም ድርጅታዊ መዋቅሩን አጠናክሯል። በሃገር ውስጥ በራሱ በወያኔ ድርጅት፣ በጭፍሮቹ እና በሠራዊቱ ውስጥ የግንቦት7 መዋቅር ሥር ሰዷል። በውጭ አገራት ደግሞ ኢትዮጵያዊያን በሚገኙባቸው አገሮች ሁሉ የንቅናቄያችን መዋቅሮች ተዘርግተዋል። የጋዜጣና ሬድዮ ዝግጅቶቻችንም ጥራት ለማሻሻል በርካታ ተግባራዊ እርምጃዎች ተወስደው ውጤታማ ሆኗል።
2. በፓለቲካ ፓርቲዎች የእርስ በእርስ ሽኩቻ የተሰላቸው ኢትዮጵያዊ በግንቦት7 መምጣት እየተነቃቃ ነው። የፓለቲካ ድርጅቶችም ወድ ኅብረት እየመጡ ነው። የትብብር መሠረቱም ወያኔን በማስወገድ ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ወያኔን የመጨረሻ የኢትዮጵያ አምባገነን ለማድረግ ያለመ እና የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት በሚያረጋግጥ መልክ መሆኑ ትብብሩ የበለጠ ተስፋ ሰጭ እንዲሆን አድርጎታል።
3. በዲፕሎማሲ ረገድ የአሜሪካና የአውሮፓ መንግሥታት እና የአውሮፓ ኅብረት የግንቦት7 ዓላማን እንዲረዱ የንቅናቄያችን ከፍተኛ አመራሮች በአካል ተገኝተው አስረድተዋል። በዚህም መሠረት ከባርነት ራሳችንን ነፃ ለማውጣት መቁረጣችንን እንዲያውቁት ተደርጓል።

አዲሱ ዓመት ካለፈው ለበለጠ ውጤት ዝግጅቱ ተጠናቋል። ነፃነቱንና አገሩን የሚወድ ዜጋ ሁሉ ሕይወቱን፣ ገንዘቡና ጊዜውን ሰውቶ ለውጥ ለማምጣት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገባ ጥሪዓችንን እናስተላልፋለን።

**መልካም አዲስ ዓመት!**




ጀግናው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ አገርህ በጎጠኛና በአምባገነኖች መዳፍ ስር ወድቃ ማልቀስ ከጀመረች ብዙ አመታት ተቆጠሩ። እንደገናም አዲስ የመከራ አመትን ለመቁጠር እነሆ አዲስ አመት ባተ። ዘረኞችና አምባገነኖች፣ ከአህጉር አልፎ አለምን ጉድ ያስባለውን ጀግንነትህንና አይበገሬነትህ በመፈታተን፣ ታሪክን በማንቋሸሽና ማንነትክን በማጥፋት ስራ ተጠምደው ሲከርሙ እያየህ እንዳላየህ ሆነህ ስትታገሳቸው ቆይተሀል። አሁን ግን ትእግስትህ መሟጠጡን በየጊዜው ከምትወስዳቸው እርምጃዎች እየተመለከትን ነው።

ለ19 አመታት ሲናድና ሲጠገን የኖረውን መርዘኛና ሂትለራዊ አገዛዝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቅበር እና በአገራችን ዲሞክረሲያዊ አስተዳደር ለመመስረት፣ የሁሉንም ርብርቦሽ ይጠይቃል።




የግንቦት 7 ንቅናቄ በአዲስ ዓመት አዳዲስ ታሪካዊ ድሎችን ለማስመዝገብ ጠንክሮ በመስራት ላይ ነው። እርሰወም ይህችን አገር ለመታደግና ከባርነት አገዛዝ ነጻ ለማውጣት የግንቦት 7ት ንቅናቄ ላቀረበውን ጥሪ እሁንኑ ምላሽ ይስጡ። አብረውን ታሪክ ይሰሩ፣ ታሪክዎንም በደማቁ ብዕር ይጻፉ።

**መልካም አዲስ አመት።**

# የግንቦት 7 ሊ/መንበር፣ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ለመሆኑ ስለወደፊቱ የአገራችን ሁኔታ ጥሩ ስሜት ይሰማናል፤ ጥሩ አቅጣጫ ይታየናል?"

ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡት መልስ አሉታዊ መሆኑን በሀዘንና በቁጭት የሚናገሩት ሊ/መንበሩ ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡም፤ "የቸገረንና ሁኔታውን እጅግ አሳሳቢ የሚያደርገው ከሞላ ጎደል በሁሉም አቅጣጫ፤ ማለትም በኢኮኖሚው፤ በፖለቲካውና በማህበራዊው ዘርፍ ካለፈው የተሻለንበት ሁኔታ አለመፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ነገሮች በአደገኛ ሁኔታ እያደር ይበልጥ እየተበላሹ መሄዳቸው ነው:: ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ በማህበረሰባችን ላይ የሚመጣው ጣጣ ማለቂያ የሌለው መሆኑ፤ እነመለስ ካደረሱን የገደል ጫፍ ላይ ተረባርበንና ተያይዘን መመለስ ካልቻልን ገደሉ ውስጥ ገብተን ከተከሰከስን በሁዋላ መመለሻ ስለሌለው ነው ይህንን ችግር ለአንዴና ለሁሌ ለመንቀል በፍፁም የአስቸኳዋይነት ስሜት ታጥቀን መነሳት ያለብን" ይላሉ።

> **ይህ የዛሬው የአዲስ አመት መልእክት የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የመጨረሻው መጀመሪያ እምቢልታ የተነፋበት ነው:: ባጠቃላይ ከሀዘንና ከንፈር ከመምጠጥ ወጥተን እያንዳንዳችን በተግባር ትንሽም ብትሆን ጠጠር የምንወረውርበት ጊዜ መጀመሪያ ነው:: በያካባቢው የሚገኙ የነፃነት ታጋዮች የሚያደርጉትን በእንቅስቃሴያቸው ታያለህ:: የምትችል ሁኔታህን ካመቻቸህ በሁዋላ ተቀላቀላቸው:: የማትችል መረጃ በማቀበል፤ ቢጠማቸው ውሀ በማጠጣት፤ ቢርባቸው በማብላት መደበቅ የሚፈልጉትን በመደበቅ ተባበራቸው::**

ሊ/መንበሩ ባለፈው አመት ከተከናወኑ ድርጊቶች መካከል፣ ሁሉም ማለት ይቻላል፣ ፍሬ አልባ ተክሎች መሆናቸውን አንዳንድ ምሳሌዎችን በመጠቃቀስ አቅርበዋል፤ "በግብርናው ምርት ማደግና በገበሬው ሀብታምነት ላይ የተመሰረተ ነው የተባለለት የኢኮኖሚ እድገት እያደር እየጨመረ በሄደው የገበሬ ረሀብተኛ ብዛት የወያኔን ውሸት ሊያምኑለት ለሚፈልጉት ፈረንጆች እንኳዋን የማይዋጥ ሆኖአል:: በውጭ ምንዛሪ እጥረት፤ በብድር ገንዘብ መጥፋት፤ በከተሞች በተንሰራፋው አስከፊ ድህነት ምክንያት ገበያተኛ በመጥፋቱ፤ በመብራት መቋዋረጥ፤ በውሀ እጥረት፤ ሆን ተብሎ በተፈጠረ የዋጋ ንረት፤ ባለሀብቱን ከጨዋታው ለማስወጣት አገዛዙ በሚያስቀምጠው መረን የለቀቀ የዝርፊያ ታክስና: በአለም ላይ የተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ ተደማምረው የከተማው ኢኮኖሚ ከሞላ ጎደል ባለበት መቆሙን፤ የአገራችን ነጋዴዎች በድፍረት የሚናገሩበት፤ ፈረንጆቹም በየጋዜጦቻቸው በግልፅ የሚፅፉበት ደረጃ ላይ ተደርሶአል::የስልጣን እድሜው ከማለቁ በፊት የአገሪቱን ሀብት በቶሎ ለመቀራመት ሲል፤ ለአገሪቱ ዘላቂ መርዝ ጥሎ የሚያልፈውን አገሪቱን በኦፊሴልና በኢንቬስትመንት ስም ሸንሽኖ መሸጥን እንደ ትልቁና አዲስ ግኝት አድርጎ ይዞታል:: ከየት እንደሚያመጣው ገና ያልታወቀውንና መሬቱ እንኳዋን ቢኖር ምን አይነት ዘላቂ አካባቢያዊ የብዙሃ ሕይወት ችግር እንደሚያስከትል ሳያሰላ፤ መሬት ለአዲሶቹ የእስያና የመካከለኛ ምስራቅ ወዳጆቹ መቸብቸብ ፈለገ:: ይታያችሁ ይህ አገዛዝ በመሬት ጥበት የሚሰቃዩ ኢትዮጵያውያን በመጠኑ መሬት ወደሚገኝበት ሌላ የአገሪቱ ክፍል ሄደው እንዳያርሱ በክልል ኬላ አቁዋቁም አጥብቆ የሚከለክል አገዛዝ ነው::"

በፖለቲካዊው መስክ ስለታዩት ችግሮች ሲገልጹ ደግሞ እንዲህ ይላሉ "የኢትዮጵያ ህዝብ የዘንድሮውን አዲስ አመት የሚያከብረው በጭለማ ተውጦ መሆኑን እናውቃለን። ጭለማ ስንልም የኤሌክትሪክ ብርሃን እጦትም ብቻ ሳይሆን፣ የአዲስ ተስፋ እጦትም እየተፈታተነው መሆኑም ግልፅ ነው። በግንቦት 97 ምርጫ በህዝብ ድምፅ የተረታው ወያኔ፣ ራሱን በስልጣን ለማቆየት በወሰዳቸው መጠነ ሰፊ የእመቃና የአፈና ተግባራት፣ ለመከላከያ ሃይሉ፣ ለሰላዮቹ፣ ለጠባብ ብሄርተኛ የፈሪ ስትራተጂው፣ ለሙስናውና ለገንዘብ ማሸሹ ተግባራት ለማውጣት የተገደደው ወጪ ከሃገሪቷ አቅም በላይ መሆኑ አንዱ ምክንያት ነው ።

አዎን ወያኔ በግንቦት 97 የደረሰበትን ሽንፈት ለማድበስበስና፣ በሃገር ብሄርተኝነት ስም የህዝብን ድጋፍ የሚያገኝ መስሎትም ሆነ፣ ከቡሽ አስተዳደር የገንዘብ ድጎማ አገኛለሁ በሚል ስሌት፣ ሰራዊቱን ሶማልያ ውስጥ በማስገባት በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ወንጀል ከመፈፀሙም ባሻገር፣ የድሃ ሃገራችንን ሀብት አላስፈላጊ የሆነ ጦርነት ላይ በማባከን ለሃገር ዕድገት ሊውል ይችል የነበረውን ብሄራዊ ሃብት በጦርነት ላይ አውድሞ፣ በሺህ የሚቆጠሩ የሠራዊቱ አባላት እንዲሞቱና አካለ ጎዶሎ እንዲሆኑ ካደረገ በሁዋላ በዚሁ ባሳለፍነው አመት ጭራውን ቆልምሞ ወጥቶአል።"

"በመሃል ሃገር በእብሪት የያዘው የአናሳ ስልጣን የማከተሙ ተፈጥሮአዊ ህግ አይቀሬ መሆኑን በምርጫ 97 በተከናነበው ውርደት ስለተረዳ እሱ በስልጣን እስካለ ድረስ ምንም አይነት የሰለጠነ ፖለቲካ በአገሪቱ ሊካሄድ እንደማይችል በግልፅ፤ ፅፎ ባፀደቃቸው ሕጎችና ዝለሉ ሲላቸው በስንት ከፍታ እንጣጥ እንበል በሚሉ ወራዳ ዳኞች በሞላው ፍ/ቤቱ አሳይቶናል። በዚሁ →

ባሳለፍነው አመት" የሚሉት ሊ/መንበሩ አያይዘውም "የግል ሚዲያዎችን እውነት መናገር ወንጀል በሚያደርግ የሚዲያ ሕግ በመጀመሪያ አሰራቸው:: ቀጠለና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እግር ተወርች የሚያስር፤ በፈለገው ጊዜ ያለምንም ምክንያት ሊዘጋቸው የሚያስችለው ሕግ ብጤ አወጣላቸው:: በመጨረሻም ምናልባት በነኝህ ሕጎች የተረሳ ነገር ካለ በሚል አዲስና ሁሉን አቀፍ የፀረ-ሽብርተኛ አዋጅ ታወጀለት:: ይህኛው አዋጅ ደግሞ ማንንም ሰው (የአይኑ ቀለም ያላማረውንም) ሽብርተኛ ብሎ የመጥራትን፤ ከዚያም ላልተወሰነ ጊዜ ከማንም ጋር እንዳይገናኝ ማሰርን፤ በሰቆቃ መጥበስን፤ ንብረቱን መዝረፍን የሚፈቅድ ህግ ነው:: በአፓርታይድ ጊዜ ነጮቹ በጣም በሚንቁዋቸው ጥቁሮችና በነፃነት ተዋጊዎቹ ላይ እንኳዋን እንደዚህ አይነት ሕግ አላወጡም::"

በአገራችን ውስጥ የሚታየው የሙስና ደረጃ ልኩን ማለፉን የሚናገሩት ዶ/ር ብርሀኑ፣ ያለፈው አመት ብዙ የሙስና ተግባራትም የተጋለጡበት አመት እንደነበር ተናግረዋል"

አዲሱን አመት የምናከብረው በእስር ላይ ያሉ ታጋይ ወገኖችን በማሰብ መሆን እንዳለበትም ዶ/ር ብርሀኑ በአጽኖት ተናግረዋል "" በእስር ላይ የምትማቅቀውን የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር፣ ወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳን ሳናስብ፤ ዘረኝነትን በመቃወማቸው በሚያንገፈግፍ ሰቆቃ ውስጥ እየተጠበሱ ያሉትን እነ ጀነራል ተፈራ ማሞን፤ ልጃችሁ ወይንም ወንድማችሁ ይቃወመናል ስለዚህም እነሱን ለመበቀል አጠገባችን ያላችሁትን እንቀጠቅጣለን በሚል የሚረገጡትን የ83 አመት አባት እነ አቶ ፅጌ ሀብተማርያምንና ሌሎቹንም የሕሊና እስረኞች ሳናስብ በአሉን ማክበር አይቻለንም።"

ሊ/መንበሩ ይህን አምባገነንና ዘረኛ አገዛዝ ለማስወገድ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችም እንዲህ አቅርበዋል "

ይህ የዛሬው የአዲስ አመት መልእክት የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የመጨረሻው መጀመሪያ እምቢልታ የተነፋበት ነው:: ባጠቃላይ ከሀዘንና ከንፈር ከመምጠጥ ወጥተን እያንዳንዳችን በተግባር ትንሽም ብትሆን ጠጠር የምንወረውርበት ጊዜ መጀመሪያ ነው:: በያካባቢው የሚገኙ የነፃነት ታጋዮች የሚያደርጉትን በእንቅስቃሴያቸው ታያለህ:: የምትችል ሁኔታህን ካመቻቸህ በሁዋላ ተቀላቀላቸው:: የማትችል መረጃ በማቀበል፤ ቢጠማቸው ውሀ በማጠጣት፤ ቢርባቸው በማብላት መደበቅ የሚፈልጉትን በመደበቅ ተባበራቸው::

> **ዘረኝነት በቃን በሉ:: ለነፃነት፤ ለእኩልነት፤ ለአገር ክብር በሚታገሉ ወገኖቻችሁ ላይ በትር አታንሱ::**

ከዚህ በተጨማሪ ግን በራስህ ከዚህ የሚከተሉትን እርምጃዎች በግልፅ ሳታወጣ/ሳታወጪ በውስጥህ/በውስጥሽ ወስነህ/ወስነሽ በግልህ ውሰድ/ውሰጂ፡

1. ከማናቸውም የወያኔና የተለጣፊዎች የፓርቲ የንግድ የዝርፊያ ድርጅቶች፤ ወይንም በግለሰብ ስም እያደርጉ ከሚዘርፉት ድርጅቶቻቸው፤ ወይንም ከታወቁት ከነሱ አጋር ነጋዴዎች ጋር ምንም አይነት የንግድ ውልም ሆነ የምርት መጠቀም አታድርግ::

2. የመንግስት ሰራተኛ የሆንሽው በስራሽ ላይ ለግሚ፤ በቀን ሰርተሽ የምትጨርሺውን ስራ ሳምንት አቆይው:: በመስሪያ ቤትሽ የሚደረገውን ዘረፋ፤ ሚስጥር ወይንም ማናቸውም ይጠቅማል ብለሽ የምታስቢውን መረጃ አንቺን በማያጋልጥ መልኩ ለነፃነት ታጋዮች አሳልፊ::

3. እያንዳንዱ ነፃነቱን የሚናፍቅ፤ ዘረኝነት ያንገሸገሸው ኢትዮጵያዊ በከተማም ሆነ በገጠር በቅርብ ከሚያውቃቸውና ከሚያምናቸው ጉዋደኞቹ ወይንም ዘምዶቹ ጋር ብቻ በመሆን ከሶስት እስከ አምስት እራሱን ሆኖ ህዋስ ይፍጠር:: ይህ ህዋስ ዝም ብሎ ስለአገሩ ጉዳይ ምን ማድረግ እንችላለን ብሎ የልቡን የሚወያይበት፤ በነፃነት ታጋዮች መገናኛ ብዙሀን የሚሰማውን ዜና የሚወያይበት፤ የሚቀርቡ ተግባራዊ ጥሪዎችን ተከታትሎ ምንም ሳይናገር ባካባቢው ተግባራዊ መሆናቸውን የሚከታተልበት፤ የአካባቢውን መረጃ ለነፃነት ሀይሎች የሚያቀብልበት በማህበራዊ ኑሮው የዘረኝነትን ሰንኮፍ የሚነቅልበት ህዋስ ነው::

4. አምነህበት ሳይሆን ለኑሮ ብለህ ወያኔ/ኢሕአዴግን የተቀላቀልክ፤ በተለይ አባል ካልሆንክ ስራ አትሰራም ተብለህ በውዴታ ግዴታ የገባህ፤ በግልህ ልብህ የሚፈልገውን በነፃነት የመኖር ጥም ለማርካት ከነፃነት ሀይሎች ጋር ብዙ ልትተባበር ትችላለህ:: ከሌላውም የበለጠ የማታምንበት ድርጅት ውስጥ በማስገባት ያዋረዱት አንተን ነውና ውርደትህን በሆድህ ይዘህ፤ እልህህን እነሱን ለመገዝገዝ ተጠቀምበት:: በመጀመሪያ ባካባቢህ የሚገኙ ዜጎችን አትበድል:: አባል በመሆንህ የምታገኛቸውን ሚስጥሮች አሳልፍ፤ የነፃነት ሀይሎች አደጋ ላይ የወደቁ ሲመስልህ አስታውቃቸው፡ በአካባቢህ ከሚኖሩ ዜጎች ጋር የሰላምና የመተሳሰብ ኑሮ ኑር:: **ወደ ገጽ 4 ዞሯል**

# የግንቦት 7 ሊ/መንበር፣ ዶ/ር ብርሀኑ ነጋ . . . ከገጽ 3 የዞረ

5. የኢትዮጵያ ወታደሮች፤ ፖሊሶች፤ ደህንነቶች ወይንም ማናቸውም ይህን ዘረኛ መንግስት መስሎአችሁም ሆነ ተገዳችሁ የምታገለግሉ ኢትዮጵያውያን፡፡ ዘረኝነት በቃን በሉ፡፡ ለነፃነት፤ ለእኩልነት፤ ለአገር ክብር በሚታገሉ ወገኖቻችሁ ላይ በትር አታንሱ፡፡ በኢትዮጵያ ድሀ ህዝብ ታክስ እየተከፈለህ ጥቂት ዘረኞችን በስልጣን ለማቆየት ብለህ ከወገንህ ጋር ዘላቂ ቂም ውስጥ አትግባ፡፡ ለፖለቲካ ችግሮቻችን ፖለቲካዊ መፍትሄ ለፖለቲካ ችግሮቻችን ፖለቲካዊ መፍትሄ እንዳንፈልግ በትእቢት ሁሉንም ረግጠን እንገዛለን ብለው የሚመኩት አንተን ከወገንህ ጋር ደም በማቃባት ነው፡፡ ነገ ዕጣህ እንደ ቀድሞዎቹ “የደርግ ወታደሮች” ሜዳሊያህን በየቤተ-ዕምነቱ ደጃፍ አንጥፈህ መለመን እንዳይሆን፣ “እኔ የህገመንግስቱ ዘብ እንጂ የወያኔ አሽከር አይደለሁም” ብለህ እምቢ በላቸው፡፡ የነፃነት ሀይሎችን፤ የእኩልነት ሀይሎችን እርዳ፤ ተቀላቀል! ለዘረኞች ስልጣን ብለህ አትሙት!
6. ለዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መወለድ ጉልህ ሚና ከሚጫወቱት መሃል፣ የሙያ ማህበራት፣ የፆታ ድርጅቶች፣ የመፅሃፍት ክበባት፣ የወጣትና የተማሪዎች ማህበራት፣ የሰራተኞች ማህበራት ወዘተ ናቸው ። በዚህ የአዲስ አመት በአል ጅማሮ ላይ፣ ኢትዮጵያውያን፣ በመሰሏቸው የሙያና በፍላጎቶች ነፃነታቸውን አስከብረው፣ በሃገራዊ ጉዳዮችም ሆነ፣ በተናጠል ነገሮች የመምከርና ድርጅታዊ አቅምና ልምድ የማካበት መብት በተለይ የገናናው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ወራሾች የሆኑ የሁሉም ብሄረሰቦች ተማሪዎች፣ የዘረኞች መሳሪያ እየሆነ ያለውን የብሄረሰብ ተማሪ ማህበራት ተንኮልና ድቀት ተሻግረው፣ እንደ አንድ ዜጋ እንዲቆሙና እንዲደራጁ ጥሪ አደርጋለሁ ።”

በመጨረሻም ሊ/መንበሩ ለኢትዮጵያ ህዝብ የአደራ ቃል በመስጠትና መልካሙን ሁሉ በመመኘት ንግግራቸው ደምድመዋል “ ለኢትዮጵያ ህዝብ በአዲስ አመት ማዕዳችን ዙሪያ ስንሰበሰብ፣ ለዘረኞች ላለመንበርከክና፣ ህይወታችንን የመለወጥ አቅም በእጃችን እንዳለ አምነን፣ ለልጆቻችን ከተረከብናት የተሻለች ኢትዮጵያን ትተን ለማንቀላፋት፣ ፈጣሪያችን ብርታቱን እንዲሰጠን እንፀልይ። አጥብቀን ከሻነው፣ ከህልም ገነታችን እንድንደርስ የታወቀ ነው ። የምንፈፅመውም ትልቅ ሃጢአት ቢኖር፣ ከማለም ተቆጥበን፣ መፃኢቱን ኢትዮጵያ፣ በዐይነ ህሊናችን ማየት የተሳነን ቀን ነው ። የተሻለ ማድረግ እንችላለን ። እንደ ገብረዬ “ካልተሳካልኝ ይልቅ፣ ያልሞከርኩት ነው የሚቆጨኝ” ብለን፣ ወዳለፈው ውድቀታችን ማተኮር ሳይሆን፣ በህሊናችን ሃይል ተስበን ልናዋልዳት ስለምንጨነቅላት የኢትዮጵያችን ተስፋ ከማለም እንዳንቆጠብ፤ ሕልማችንን እውን ለማድረግ ደግሞ በተግባር ማድረግ ያለብንን ሁሉ እንድናደርግ አደራ እላችሁዋለሁ። በአዲስ አመት ከዚህ የበለጠ አደራ መጠየቅም አይቻልም ።

## በግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የተዘጋጀ

org@ginbot7.org
P.O.Box: 4916, 2003 EX, Harlem, The Netherlands
Tel: +44 208 133 5670

## የ፳፻፪ (2002) ዓም የቀን መቁጠሪያ

### መስከረም

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1 | 2 | 3 |
| 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | |

1 አዲስ አመት
11 ኢድ አልፈጥር
17 መስቀል

### ጥቅምት

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | | | | | | |

### ህዳር

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 28 | 29 | 30 | | | | |

2 በወያኔ የኢ.ጋዜ. የተፈጸ የዴሞክራሲ ሰማእታት ቀን
19 ኢድ አልአድሃ

### ታህሳስ

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

29 የገና በአል

### ጥር

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

11 ጥምቀት

### የካቲት

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | | | | | |

### መጋቢት

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | | | |

24 ስቅለት
26 የፋሲካ በአል

### ሚያዚያ

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 1 | 2 | 3 |
| 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | |

30 ታላቁ የዴሞክራሲ ትእይንተ ህዝብ በአዲስ አበባ

### ግንቦት

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | | | | | | |

20 ዘረኞች ኢትዮጵያን የተቆጣጠሩበት
7 የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ ቀናኢነቱን ያረጋገጠበት
7 የግንቦት 7 ንቅናቄ የተመሰረተበት እለት

### ሰኔ

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 28 | 29 | 30 | | | | |

1 በወያኔ ህይወታቸው የተቀጠፉ የሰማእታት ቀን

### ሐምሌ

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

### ነሐሴ

| M | T | W | T | F | S | S |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

### ጳጉሜ

| M | T | W | T | F |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

16 ረመዳን

www.ginbot7.org


# የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ

## የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።


**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org